# ግብጻዊያኖች የሚያዛልቀውን መንገድ

# አሁን መረጣችሁ!

ለገሰ አስማማው

07/08/14

ሰሙኑን የተለያዩ ሚዲያዎችን ስመለከት አዲሱ የግብጽ መንግስት ባለስልጣናት በህዳሴው ግድብ በተመለከተ የቀድሞዎቹ ባለስልጣናት ያራምዱ የነበረውን "እኛ ብቻ እንጠቀም" አካሄድ እንደማያዋጣ በመገንዘባቸው ወደ ጋራ ተጠቃሚነት የሚያመራውን ቀና መንገድ የመረጡ ይመስላሉ። አልሲሲ የኢትዮጵያና የግብጽ ውዝግብ በፍጥጫ መፍትሄ ሊያገኝ እንደማይችል በመረዳታቸው የሁለቱን አገራት ግንኙነት ሊያጠናክሩ የሚችሉ አካሄዶችን እየተከተሉ እንደሆነ አንዳንድ ነገሮች እየጠቆሙ ናቸው።

ለዚህም ይመስላል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ የግብጽ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት እየተሳተፉ እንደሚገኙ ማየት ይቻላል። ባለፈው ሳምንት እንኳን የሁለቱን አገራት ኤኮኖሚያዊ ትስስር እነዲጠናከር ለማድረግ የግብጽ የግብርና ሚኒስቴር በረመዳን ጾም ወቅት ለሥጋ የሚሆን የቀንድ ከብት ከኢትዮጵያ በመግዛት ለህዝባቸው በተመጣጠነ ዋጋ ለማከፋፈል መወሰናቸውን የተለያዩ ሚዲያዎች ዘግበዋል። በዚህም መሠረት ከዚህ ሳምንት ጀምሮ እስከ አረፋ መጨረሻ ድረስ ከኢትዮጵያ 40 ሺህ የሥጋ ከብቶችን ከኢትዮጵያ እንደሚገዛና በተለያዩ የግብጽ ከተሞች እንደሚያከፋፈል የግብርና ሚኒስቴሩ አስታውቋል።

በተመሳሳይ ግብጽ ለጥቁር አምበሳ ሆስፖታል የልብ ህክምና ማዕከል ዘመናዊ የህክምና መሳሪያ በእርዳታ መስጠቷም ሌላው የሰሞኑ ክስተት ነበር። መሳሪያው የተበረከተው በግብጽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሚገኘው የግብጽና ከአፍሪካ ቴክኒካዊ የትብብር ፈንድ እና የግብጽ ዓለም አቀፍ የልብ ቀዶ ጥገና ሀኪም ከሆኑት ከፕሮፌሰር መጅዲ ያዕቆብ ጋር በመተባበር መሆኑን በኢትዮጵያ የግብጽ አምባሳደር መሀመድ እንድሪስ የህክምና መሳሪያውን ለሆስፒታሉ ባስረከቡበት ወቅት ይህ ስጦታ በወንድም የኢትዮጵያና የግብጽ ህዝቦች መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት ይበልጥ ያጠናክረዋል ብለዋል። ይህ አይነት አካሄድ የሁለቱን አገራት የህዝቦች  ግንኙነት እደሚያጠናክረውም አምባሳደሩ አያይዘው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያና የግብጽ ለዘመናት በበርካታ ጉዳዮች ላይ ጥብቅ ግንኙነት ያላቸው አገሮች እንደሆኑ በርካታ ማስረጃዎችን ማንሳተ ይቻላል። ይህን የሁለቱን አገሮች ግንኙነት በተመለከከተ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ  "ፍቺ ሊፈጸምበት የመይቻል ትዳር"  ሲሉ የሁለቱን አገራት ቁርኝት ገልጸውታል። አዎ ኢትዮጵያ  ለግብጽ የህይወት ምንጭ የሆነው ውሃ መፍለቂያ ሆና ሳለ ሁለቱ አገራት ሊነጣጠሉ፣ አንደራረስ ብለው ሊማማሉ ከቶ አይቻላቸውም። ይሁንና ይህን የጠበቀ ግንኙነት ያላቸውን አገሮች ለመነጣጠል የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱን ለማሻከር አንዳንድ  የግብጽ ሚዲያ ባለሙያዎች፣ የቀድሞ ባለስልጣናትና ምሁራን አፍራሽ ዘመቻዎች ሲናፈሱ  ቆይተዋል።

የቀድሞዎቹ የግብጽ ገዢዎች የአባይ ወንዝ ጉዳይን በአገሪቱ ውስጥ ለሚነሱ የፖለቲካ ጥያቄዎች የመሸፋፈኛ መሳሪያ በማድረግ ሲጠቀሙበት ኖረዋል፡፡ ከእነዚህ መሪዎች መካከል በህዝባዊ አመጽ ከስልጣን መንበራቸው የተወገዱት ሁስኒ ሙባረክና ሙሃመድ ሙርሲ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ መሪዎች ግብፃዊያን ከአባይ ወንዝ ውጭ ህይወት የላቸውም፤ ከአባይ ጋር በተያያዘ ግብፅና ግብፃዊያን አደጋ ውስጥ ናቸው በሚል የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት የአገሪቱን ዜጎች በስጋትና በጥርጣሬ ውስጥ እንዲጠመዱ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ይህንን ውሃ ጥቅም ላይ በማዋል የግብፃዊያን ህልውና አደጋ ላይ የመጣል ግብ አላት የሚል

እውነተኝነት የራቀውን ስብከት በመንዛትም ግብፃዊያን በኢትዮጵያ ላይ የተሳሳተ አመለካከት እንዲፈጥሩ በማድረግ ህዝቡ በውጭ ጉዳይ እንዲጠመድና የውስጥ ጉዳዩን እንዳያይ አድርጎት ቆይቷል።

ባለፉት ጥቂት አመታት የግብጽ አካላት በሚከተሉት በየጊዜው በሚቀያየር አቋም አባይን በተመለከተ የግብጽ አቋም ምን እንደሆነ መረዳት የሚያስቸግርበት ሁኔታ ነበር። ከአልሲሲ በፊት የነበሩት የቀድሞው የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ መሪ የነበሩት ሙሃመድ ሙርሲ ተካፋይ የነበሩበት በቀጥታ ስርጭት ይተላለፍ በነበረ የቴሌቭዥን ውይይት ላይ ኢትዮጵያ የህዳሴው ግድብ የምትገነባው ግብጽን ለመጉዳት በመሆኑ ግድቡን በቦንብ እናጋየዋለን የሚል ቀረሮ በየአደባባዩ ሲሰጡ ተደምጠዋል። ይሁንና ይህ አካሄድ ያላቸውን አቅም አገናዝበውም ይሁን ወይም አለም አቀፍ ሁኔታዎችን ከግምት ወስደው አዋጪ መንገድ ያለመሆኑን በመረዳት ሊገፉበት አልፈለጉም።

ሌላው በግብጻዊያን ኢትዮጵያ የህዳሴውን ግድብ መገንባት እንዳትችል ለማድረግ እንደተመራጭ መንገድ የተያዘው ነገር ኢትዮጵያዊያን የተከፋፈሉ በውስጥ ችግራቸው የተተበተቡ በመሆናቸው በቀላሉ ልንበታትናቸውና ልናተራምሳቸው እንችላለን የሚል አካሄድ ነበር። ይህንንም መንገድ ሳይሞክሩት የቀሩ አልመሰለኝም። እንደ ኦብነግ፣ ኦነግና ግንቦት ሰባት ያሉ ህዝባዊ ድጋፍ የሌላቸውን አካላት ለማሰባሰብና የአትዮጵያን ሰላም በማወክ፣ ይህን በቢሊዮን የሚቆጠር ፕሮጀክት ማካሄድ እንዳትችል ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ነበር። ይሁንና የኢትዮጵያ መንግስት ጠንካራ መሰረት ያለውና ጠንካራ ህዝባዊ ድጋፍ ያለው መሆኑን በመረዳታቸው ሊገፉበት አልቻሉም። የታላቁ የህዳሴ ግድብ የህዝብ ፕሮጀክት በመሆኑ  በእነኦብነግ፣ ኦነግና ግንቦት ሰባት ጸረህዝብና ጸረልማት ሃይሎች ከቶ ሊደናቀፍ እንደማይችል ሊታወቅ ይገባል።

ሌላው አማራጭ ብለው የያዙት መንገድ ነውጠኛ የሆኑ የአካባቢው አገራት ያሉ ሃይላትን በማደራጀት የቀጠናውን ጸጥታ ማወክ ነበር። በዚህ ጉዳይ በጥሩ አማራጭነት የተወሰዱት ነውጠኛው የኤርትራ መንግስትና አሸባሪው አልሸባብ ናቸው። የኤርትራ መንግስት በቀጥታ ጦርነት ወይም የውክልና ጦርነት ውስጥ

ቢገባ በቆፈረው ጉድጓድ ግበዓተ መሬቱን መፈጸም መሆኑን በማወቁ ከዚህ ጉዳይ እጁን መሰብሰቡን መርጧል። የኤርትራ መንግስት በቀጥታ ጦርነት ውስጥ መግባትን ይፍራ እንጂ ተቋዋሚ ነን የሚሉ ደካማ ሃይሎችን በማሰባሰብ፣ በማሰልጠንና ወደ ኢትዮጵያ በማስረግ ችግር ለመፍጠር አልቦዘነም። ይሁንና እቅዱ ሁሉ በህዝብና በደህንነት ሃይሉ ቀድመው በመመታታቸው የተፈለገውን ውጤት ማስገኘት አልቻሉም።

ግብጻዊያን ባለስልጣናት ሌላ አማራጭ አድርገው ይንቀሳቀሱበት የነበረው ጉዳይ ኢትዮጵያ ይህን በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በራሷ አቅም መገንባት አትችልም። ስለዚህ ብድርና እርዳታ ልታገኝ የምትችልባቸውን መንገዶች መዝጋት አለብን በሚል የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርጉ ነበር። ግብጻዊያን ባለስልጣናት ለኢትዮጵያ ብድር ወይም እርዳታ ሊሰጡ ይችላሉ ወደሚባሉ ተለያዩ የምዕራቡም ሆነ የምስራቁ አገራት በመንከራተት ብድርና እርዳታ ለኢትዮጵያ መንግስት እንዳይሰጡ በማለት ሲማጸኑ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

ይሁንና ኢትዮጵያ ይህን ሁኔታ ቀድማ ተገንዝባው ነበር፤ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትራችን “ የገንዘብ ምንጮቹም እኛው ግንበኞቹም እኛው” በማለት የገለጹት። በውጭ በብድርና ዕርዳታ ላይ ተንጠልጥለን ይህን ግድብ ጀምረነው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ላይ የግብጾች እቅድ ይሳካላቸው ነበር። ይሁንና የኢትዮጵያ መንግስት ሁኔታውን ቀድሞ የተገነዘበው በመሆኑ ታላቁን የህዳሴ ግድብ በራሳችን አቅም ለመስራት መወሰኑ ግንባታው በማንም ተፅዕኖ ስር እንዳይወድቅ አድርጎታል።

ሌላው ግብጻዊያን በአማራጭነት የያዙት አካሄድ በኢትዮጵያ የሃይማኖት አክራሪነትን በማስፋፋት አገሪቱን ወደብጥብጥ ለማምራት የሚያስችሉ ነገሮችን በማራገብ ነበር። አንዳንድ በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የአገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለይ እንደ ሰማያዊ ፓርቲ ያሉት የሃይማኖት አክራሪዎችን ጥያቄዎች ትክክለኛ የፖለቲካ ጥያቄዎች እንደሆኑ በማድረግ አክራሪነትን በይፋ ሲደግፉ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

ይሁንና የአገራችን ህዝበ ሙስሊም የእነዚህን ፓርቲዎች አካሄድ በመረዳቱ ድጋፉን ስለነፈጋቸው እነ ሰማያዊ ፓርቲ ድብቅ አጀንዳ ሊጋለጥ ችሏል። በኢትዮጵያ የሃይማኖት ጥያቄዎች በህገ-መንግስቱ በግልጽ ተመልሰዋል። በኢትዮጵያ ሃይማኖትና ፖለቲካን የሚለያይ መስመር የተሰመረበት ሁኔታ አለ። እባካችሁ የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች ይህን ግልጽ መስመር ተመልከቱት። አክራሪነት አገርንና ህዝብን የሚጎዳ ብቻ ሳይሆን ለእናንተም ለራሳችሁም የሚበጅ አካሄድ አየደለም።

ግብጻዊያኖች ሲሞክሩት የነበረው ሌላው አካሄድ በተፋሰሱ አገራት መካከል ያለውን ትብብር ለማዳከም የተለያዩ ነገሮችን ሲያካሂዱ ቆይተዋል። በተለይ ግብጻዊያን የሱዳናዊያኖችን ድጋፍ ለማግኘት ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ይሁንና ሱዳንያዊያኖች የአገራቸውን ጥቅም በማየት ለኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በይፋ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። የቀድሞዎቹ የግብጽ መንግስታት የህዳሴውን ግድብ ፖለቲካዊ ጉዳይ በማድረግ የአረብ አገሮችን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ የእስራኤል እጅ እንዳለበት በማድረግ ሲያናፍሱ ነበር። ይሁንና ኢትዮጵያ ትክክለኛውን ሁኔታ ለአለም ማሳወቅ በመቻሏ የትኛውም የግብጽ አካሄድ ሳይሰምር ቀርቷል።

ግብጽ በቅርቡ በካሄደችው ምርጫ አዲስ መሪ በመምረጧ አዲሱ ፕሬዝዳንት በህዳሴው ግድብ ምክንያት ከኢትዮጵያ ጋር እሰጣገባ መግጠሙ አዋጪ አለመሆኑን በመገንዘባቸው ወደ ስምምነት የሚያመሩ መንገዶችን እየተከተሉ ይመስላሉ። የታላቁን የህዳሴ ግድብን በተመለከተ በሁለቱ አገሮች መካከል እስካሁን ያለመግባባት እንዲሰፍን የግብጽ በባለስልጣናትና ምሁራኖች የሚሰጡ የተሳሳቱ አስተያየቶችን የሚዲያ ባለሙያዎች በማነፍነፍ በማይገባ መንገድ በማቅረብ በግብጻዊያን መካከል የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲፈጠር አድርገዋል።

በቅርቡ አንድ የግብጽ ቴሌቭዥን ጋዜጠኛ በግብጽ የኢትዮጵያ አምባሳደር የሆኑትን አምባሳደር ሙሃሙድ ድሪርን በህዳሴው ግድብ ዙሪያ የተለያዩ ጥያቄዎችን ስታቀርብላቸው ነበር። ጋዜጠኛ ራኒያ በደዊ በካይሮ ከኢትዮጵያ አምባሳደር ማህሙድ ድሪር ጋር ባደረገችው ውይይት የሃሳብ አለመግባባት

በመፈጠሩ ስልኩን እጆሯቸው ላይ በመዝጋት የግብጽ የውሃ እጣ ፈንታ አደጋ ላይ ነው ስትል አስታወቀች።

በስልክ ውይይታቸው ጋዜጠኛዋ አምባሳደሩን "ስለህዳሴው ግድብ የምታነሳው ጥያቄ ፖለቲካዊ ነው፤ በሀገራት መካከል የሚደረግ ውይይት ደግሞ በግፊት መሆን የለበትም" በማለቷ ምክንያት አምባሳደሩ "አንቺ ስለህዳሴው ግድብ የምታውቂው ነገር የለም፤ ንግግርሽ የበላይነትን ያሳያል" በማለታቸው፤ ጋዜጠኛዋ ደሲፒሊን በጎደለው አኳኋን አምባሳደሩን ገደብህን አልፈሃል፤ የዲፕሎማሲያዊ አካሄድን አልጠበክም እንደውም ዲፕሎማሲያዊ አካሄድን የምታውቅ አይመስልም በማለት እጆሯቸው ላይ ስልኩን ዘግታባቸዋለች።

አምባሳደሩ የደረሰባቸውን በደል ጠቅሰው ለግብጽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መልዕክት በመላካቸው አዲሱ የግብጽ መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር መልካም ግንኙነት ለመመስረት ደፋ ቀና በሚልበት ሰዓት እንዲህ ያለ ነገር በመፈጠሩ ይቅርታ ጠይቆ ጋዜጠኛዋን የገደብሽን አልፈሻል የጋዜጠኛ ስነምግባር አልተከተልሽም በሚል ከስራዋ እንድትታገድ አድርጓታል። ይህ ነው ለመልኳም ግንኙነት ሲባል የሚወሰዱ አዎንታዊ ነገሮች። አዎ የግብጽ ሚዲያዎች አካሄዳቸውን ሊያስተካክሉ ይገባል።

ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ የመጠቀም ሙሉ መብት ያላት ቢሆንም ይህንን መብቷን ሌሎቹን የተፋሰሱ አገራት በሚጎዳ መልኩ ተግባራዊ የማድረግ ምንም ዓይነት ፍላጎት እንደሌላት በተለያዩ ጊዜያት የመንግስት ከፍተኛ ሃላፊዎች አስታውቀዋል፡፡ የህዳሴው ግድብ ለተፋሰሱ አገራት የኤሌክትሪክ ሃይል ከማስገኘቱም ባሻገር የወንዙን ስነምህዳር በማስጠበቅ ዘለቄታዊ ጥቅም እንዲሰጥ እንደሚያስችለውም የዘርፉ ባለሙያዎች አረጋግጠዋል፡፡ የህዳሴው ግድብ መገንባት በታችኛው የተፋሰስ አገራት ላይ በየጊዜው የሚደርሰውን የጎርፍ አደጋ ከማስቀረቱም ባሻገር በተለይ ለሱዳን ለከፍተኛ ወጪ የሚዳርገውን ደለል ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ የሚያስገኝ ነው፡፡

ግብጽና ሱዳን ከግድቡ ከሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል በተመጣጣኝ ክፍያ አገልግሎት የሚያገኙበት ሰፊ እድል እንደሚኖርም ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ስትገልጽ ቆይታለች፡፡ ግድቡ የወንዙን የውሃ አመታዊ ፍሰት የተስተካከለ በማድረግ ረገድም ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው ባለሙያዎች ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት የህዳሴው ግድብ ስፍራ ከታችኛው የተፋሰሱ አገራት ካሉ ግድቦች በአንጻራዊነት ደጋማ አካባቢ የሚገነባ በመሆኑ በትነት የሚባክነውን ከፍተኛ የሆነ ውሃ እንደሚቀንሰው ባለሙያዎች አረጋግጠዋል፡፡

ኢትዮጵያ የህዳሴው ግድብ በምንም መልኩ የግብፅንም ሆነ የሱዳንን ጥቅም እንደማይጎዳ በተደጋጋሚ ከመግለጿም በተጨማሪ ይህንኑ ጉዳይ የሚያረጋግጥ አለም ዓቀፍ የባለሙያዎች የቴክኒክ ኮሚቴ በራሷ ተነሳሽነት እንዲቋቋም በማድረግ ለኮሚቴው ስራ መሳካትም ተገቢውንም ድጋፍ አድርጋለች፡፡ ይኸው በኢትዮጵያ፣ በግብፅና በሱዳን እንደዚሁም በዓለም አቀፍ የውሃ ባለሙያዎች ያቀፈው የባለሙያዎች ቡድን ይፋ ባደረገው ሪፖርቱ ላይ ያረጋገጠው ጉዳይ የህዳሴው ግድብ በየትኛውም የተፋሰሱ አገራት ላይ የከፋ ጉዳት እንደማያመጣ ይልቁንም የተለያዩ ጥቅሞች እንዳሉት በይፋ አመልክቷል፡፡

ኢትዮጵያ ካለባት ስር የሰደደ ድህነት ጋር የቀድሞ የግብጽ መንግስታት ያራምዱት ከነበረው አፍራሽ አካሄድ ጋር ተዳምሮ አገራችን በወንዙ ላይ ምንም አይነት ልማት እንዳታካሂድ አድርጓል፡፡ ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ ዓይነቱ የግብጽ የፖለቲካ መንገድ የማይሰራበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ማለት ይቻላል፡፡ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ኢትዮጵያ አዲስ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ስርዓት በመገንባት ጠንካራና የተረጋጋ መንግስት መመስረት በመቻሏ ነገሮች ለአንዴና ለመጨረሻ ተለውጠዋል፡፡

ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መንግስት መገንባት በመቻሏ ዘላቂነት ያለው ሰላም በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው አገራትም ጭምር እንዲሰፍን ጉልህ ሚና ተጫውታቸች። ባለፉት አመታት አገሪቱ አለምን ያስደመመ ፈጣንና ተከታታይነት ያለው እድገት ማስመዝገብ በመቻሏ ትላልቅ ፖሮጀክቶችን ሳይቀር በራሷ አቅም

መገንባት ችላለች። አገራችን ይህ አይነት አቅም በአጭር ጊዜ ውስጥ ማዳበር በመቻሏ ከጥገኝነት እንድትወጣ አድርጓታል።

በዲፕሎማሲው ረገድም የአገራችን ተደማጭነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ ኢትዮጵያችን ዛሬ ላይ ማንም እንደፈለገ እጇን ይዞ የሚጠመዝዛት አገር አይደለችም። የኢትዮጵያ መንግስት ምን መስራት እንዳለበት ሊነግረው የሚችለው ህዝብ እንጂ ማንም የውጭ ሃይል እንዳልሆነ የህዳሴው ግድብ አንድ ማሳያ ነው። ለዚህም ነው ብዙዎች የህዳሴው ግድብን ጉዳይ ከብሄራዊ ማንነት ጋር የሚያያይዙት።

ኢትዮጵያ ከሌሎች የናይል ተፋሰሱ አገራት ጋር በመተባበር ወንዙን ሁሉም ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መጠቀም ይችሉ ዘንድ የስምምነት ማአቀፍ በመፈረም አገራችን ወንዙን የማልማት ስራ ጀምራለች። ይህ ሁኔታም ኢትዮጵያ የህዳሴውን ግድብ ለመገንባት ህጋዊውን መንገድ እንደተከተለችም የሚያሳይ ነው። የኢንቴቤው ስምምነት የሚያረጋግጠው ሁሉም የተፋሰሱ አባል አገራት ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም በተፋሰሱ አገራት መካከል እንዲሰፍን በማድረግ የወዙን ድህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል ስምምነት ነው።

አንዳንድ ቀና አመለካከት ያላቸው ግብጻዊያን ምሁራን ግብጽ ስትከተል የነበረው ወንዙን በብቸኝነት የመጠቀም አቋም እንትለውጥና ከተፋሰሱ አገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ገንቢ በሆነ መልኩ ለማስተካከል መንቀሳቀስ ይኖርባታል የሚል ምክር በግልጽ ሲሰነዝሩ ተደምጠዋል፡፡ በተመሳሳይ አንዳንድ የግብጽ ወዳጅ አገራትም ግብጽ የትብብር ስምምነት ማዕቀፉን መፈረምና በኢንቪየቲቭ መሠረታዊ መርሆዎች ጥላ ስር ልዩነቷን መፍታት ይኖርባታል እንጂ በእንዲህ ያለ አካሄድ የአገሪቱን የውሃ ደህንነት ማረጋገጥ እንደማይቻል በግልጽ አስቀምጠዋል።

አንዳንድ ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ተንታኞችም በተመሳሳይ ግብጽ ቀጣይ የወንዙን ተጠቃሚነቷን ማረጋገጥ የምትችለው ሌሎች የተፋሰሱ አገራት የሚካሄዱትን የልማት ፕሮጀክቶች በመቃወም ሳይሆን ከተፋሰሱ አገራት ጋር በመመካከርና በመረዳዳት መስራት ስትችል እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ የጋራ ተጠቃሚነት መርህን

መቀበል በተፋሰሱ አገራት መካከል ጠንካራ ወዳጅነትንና መተሳሰብን በመፍጠር የአካባቢው ህዝቦች በኤኮኖሚ እንዲተሳሰሩ እንደሚያደርግም ተንታኞች ጨምረው ይመክራሉ፡፡

ኢትዮጵያ የአባይ ወንዝ ጉዳይን በተመለከተ እየተከተለችው ያለው ፍተሃዊነትን መሰረት ያደረገው ፖሊሲዋ በአካባቢው አገራትም ሆነ በአለም ያላትን ተሰሚነትን ከፍ እንዲል እንዳደረገው ብዙዎች ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡ ኢትዮጵያ የምትከተለው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በመልካም ጉርብት፣ በመከባበር፤ ለጋራ ጥቅም በመስራትና በማንኛውም አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ለመገንባት ስትነሳ የግብጽን አካድ ቀድማ በመገንዘቧ የገንዘብ ምንጭ እንዲሆን የተማመነችው የራሷንና የሕዝቧን ታላቅ አቅም እንጂ የትኛውንም የውጭ መንግስት ወይንም ዓለም አቀፍ አበዳሪ ድርጅት አይደለም፡፡ የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ግንባታ በራሷ አቅም እንደ ጀመረችው ሁሉ በሕዝቧ ታላቅ ርብርብ ለፍጻሜ ታበቃዋለች፡፡ የግድቡ ባለቤት ሕዝቡ በመሆኑም ስራውን ለማሳካት ሌትተቀን እየተረባረበ ይገኛል፡፡ ህብረተሰቡ ለግድቡ የሚያደርገው ሁለንተናዊ ድጋፍ አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ኢትዮጵያ መንግስት የህዳሴውን ግድብ ለመገንባት ሲነሳ ያራምደው የነበረው ፍተሃዊነትን መሰረት ያደረገው አቋም እስከመጨረሻው በመጽናት የመንግስታችንን ትክክለኛነትና የአቋም ጽናት የሚያሳይ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ፍተሃዊ የውሃ አጠቃቀም በአገሮች መካከል እንዲኖር ያራምድ የነበረውን ትክክለኛ አቋም ግብጻዊያን ጊዜው ሲደርስ በመረዳታቸው ቢዘገዩም የአገራችንን አቋም እየተረዱት ይመስልኛል። አገራችን ግብጽ ከገባችበት ውጥንቅጥ እንድትወጣና ወደ አፍሪካ ኅብረት አባልነቷ እንድትመለስ ከፍተኛ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች። ግብጽ ወደ አፍሪካ ህብረት መመለሷንም በተመለከተ ኢትዮጵያ ለግብጻዊያኖች የእንኳን ደስያለችሁ መልዕክት የላከች የመጀመሪያዋ አገር ናት።